# ሶቅራጥስ፤ ክርስቶስና ብርቱካን

*በላይነህ አባተ (abatebelai@yahoo.com)*

ከላይ ከርዕሱ የክርስቶስንና የሰዎችን ስም ጎን ለጎን መቀመጥ ተመልክቶ “እጅግ አበዛው!ያልሆነ ንጽጽር አመጣ” እያለ በአደባባይም ሆነ በድብቅ የሚያማ ስለማይጠፋ በቅድሚያ ለአንባቢ ይህንን ልበል። አንደኛ እነዚህ ሶስቱ እኩል ናቸው ለማለት አልዳዳሁም። በሒሳብ አለም እኩል(=) ሲባል በሁሉም ነገር አንድ የሆነ መሆኑ ይታወቃል። እንኳን አምላክና ሰዎች፤ ሰውና ሰውም ቢሆን እኩል የመኖር መብት፣ እኩል በሕግ ፊት የመታየት፣ እኩል የመማርና ስራ የመያዝ፣ እኩል ተከብሮ የመኖር፣ ወዘተ እድል ይኖረዋል እንጅ መንታ ሆኖ ከእናቱ ማህጸን እንኳ ቢወጣ እኩል ሊሆን አይችልም። ስለዚህ እንኳን ሰዎችና እየሱስ፤ ሰዎችና ሰዎችም ቢሆኑ በሁሉም ነገር እኩል ሊሆኑ፤ ሊወዳደሩም አይችሉም። ሁለተኛ አንድ አይነት ባህሪና ግብርም አላቸው ለማለት አልቃጣም። ነገር ግን በመጠኑም ቢሆን ሶስቱንም አንድ ቦታ የሚያገናኟቸው፣ በአንድ መስመር የሚያሰልፏቸው፣ በአንድ ሰንሰለት የሚያቆራኟቸው፣ በታሪካዊነት የሚዘግቧቸው ብርቱ ምክንያቶች እንዳሉ ማውሳት እፈልጋለሁ። በተጨማሪም ስለክርስቶስ ስናገር እርሱን ተከትለው መከራ ስለተቀበሉት ሐዋርያት፤ ስለ ሶቅራጥስና ብርቱካንም ሳወሳ ከድሮም ጀምሮ እንደነሱ እንዲያውም ከነሱም እጅግ በከፋ ሁኔታ እየተገደዱ የግፍን ጽዋ ስለጨለጡትና በመጨለጥ ላይ ስላሉት የሰው ልጆች ሁሉ መሆኑን መግለጽ እሻለሁ።

ሶቅራጥስን አምላክ ወይም አንዱ ሐይል ከግሪክ ምድር ላይ የጣለው ገዥዎች ሕዝብን በሐይልና በማታለል በሚያሰቃዩበት፣ የገዥዎች ሎሌዎችም ጌቶቻቸውን ለማስደሰት ዜጎቻቸውን ሰቆቃ በሚያበሉበት፣ ዜጎች ራሳቸውም እርስ በራሳቸው መተማመን አቅቷቸው በሚካካዱበት ዘመን ነበር። [1,2] እግዚአብሔር ራሱ እንደሆነ የሚታመነው ክርስቶስም ወደዚህ ምድር ብቅ ያለው ፈሪሳውያን የሙሴን መጻሕፍት እያነበነቡ የሆድ መሞያና መደሰቻ የሚያደርጉበት፣ እስራኤልን ከወረረው የውጭ ሐይል ጋር ተባብረው እየሱስን ሳይቀር እንዲሰቀል የሚያሴሩበት፣ እንኳን ሌላው እንደ ይሁዳና ጴጥሮስ ያሉት የራሱ የክርስቶስ ሐዋርያት ሳይቀር በክህደት መንፈስ ውስጥ የሰመጡበት ከንቱ ጊዜ ነበር።

አብዛኛው ኢትዮጵያዊ ስሟን እንደ መልከ ማርያም እያነሳ የሚደግማት፣ እንደ ጽገሬዳ አበባ ምስሏን አይቶ የማይጠግባት፣ እድሜዋን እንዲያረዝመውና ጤንነቷን እንዲጠብቅላት ተንበርክኮ ጠዋትና ማታ የሚጸልይላት ብርቱካንም በጦቢያ ምድር ብቅ ያለችው እንኳን ሌላው ብሉይ ኪዳንና አዲስ ኪዳንን የምናነበንብ ካህናት ማእረጋችንን ለሆድ መቆዘሪያ፣ ለስልጣን መቆናጠጫና ለሐብት ማካበቻ እያዋልን ህሊናችንን፣ ከመቀነትና ቀዳዳ ኪሱ እያወጣ በአስራት ገንዘብ የሚያስተዳድረንን ምእመናንንና አገራችንን ኢትዮጵያን እየካድን ለሰይጣን መልእክተኞች አሳልፈን በመስጠት ላይ ሳለን ነው። አዎ ብርቱካን ዱብ ያለችው ተማርን የምንል ሰዎች ለነፍሰ-ገዳዮች ደጅ ጠኝ በሆንበት፤ በራስ ወዳድነትና በስግብግብነት ወረረሽኝ በሽታ በተለከፍንበት፤ የሌላውን ደምና ፈርስ ረግጠን በሐብት ለመናጠጥ በምንቋምጥበት፤ በራሳችን ንብረት እየተሸጥን ወንድምና እህቶቻችን ያለምንም ርህራሄ ለሰይጣን መልእከተኞች አሳልፈን በምንሰጥበት፣ ቅስና፣ ምንኩስና፣ ሽምግልና፣ የመንፈስ ልእልናና ሥነ-ምግባር ወፈጥ ድንጋይ ላይ እንደወደቀ ገል ተከስክሰው በተፈረካከሱበት ወቅት ነው።

ከተፈጠሩበት የዘመን ክፋትም በላይ እነዚህን ሶስት ስሞች የሚያቆራኛቸው ሌላ ግዙፍ ሐይል አለ። አዎ! “**ቃል**” የሚባል ብርቱ ሐይል። የእየሱስ ተከታይ ነን እያልን ቆብ ከደፋን፣ ካባ ከደረብን፣ መስቀላችንን ከደረታችን ላይ ካንዠረገግን፣ በአቡንነት መንበር ላይ ከተንፈላሰስን፣ ከጵጵስና ወንበር ላይ ከተኮፈስን፣ የአስራት ንብረት እየበላን አስራት-ሰጪዎችን አሳልፈን እየሰጠን መቅደስ ውስጥ እየገባን “ከምንቀድስ” ካህናት ህሊና ላይ በእንዶድና በአመድ ታጥቦ የተጠፋ **ቃል** እነዚህን ሶስቱን ያገናኛቸዋል። እርግጥ ነው ሊቆች ነን እያልን ጣቶቻችንን እያፍተለተልን ከምንደሰኩር፣ በዲግሪና ዲፕሎማችን ፍርፋሪ እየዛቅን ሞታችንን በመጠባበቅ ላይ ካለን፤ ሽማግሌ ነን እያልን የእንጨት ሽበት ወርሶን እግራችን ወደ ጉድጓድ ላይ በመግባት ላይ ካለን፤ በሌላው ህይወት ወይም መቃብር ላይ ሥራችንን ሰደን እንደባድማ ሙጃ ለማገፍገፍ ከምንቋምጥ ጉዶች ላይ በሞራ ሳሙናና በበረኪና ታጥቦ የጠፋ **ቃል** ሶስቱን ያስተሳስራቸዋል።

ታሪክ በደማቅ ቀለም ጽፎ እንደሚያሳየን በሶስት መቶ ዘጠና ዘጠኝ አመተ-ዓለም ስለፍትህ ያስተምር የነበረው ሶቅራጥስ ቃልህን ከመብላትና ሄምሎክ(መርዝ) ከመጠጣት አንዱን ምረጥ ሲሉት ሄምሎኩን መርጦ የሚፈርሰውን ስጋ አሳልፎ ሰጥቶ ዘላለማዊውን ቃል ጠበቀ። ሶቅራጥስ ሲሞት 71 አመቱ ነበር። [1,2] መርዝ መጠታቱን ትቶ ቃሉን ቢውጥ የሚያተርፈው እድሜ በዚያ ዘመን አማካኝ እድሜ አንጻር ሲታይ ሲበዛ ቢውል ከአስር ዓመት በላይ ላይሆን ይችል ነበር። መርዙን በመምረጡ ግን የዘላለም ነዋሪ ሆኗል። ሶቅራጥስ ከሞተ ከአራት መቶ ዓመታት በኋላ በቤተልሄም የተወለደው፤ ስለሰው ልጅ ልእልና ሲሰብክ የነበረው ክርስቶስ እንደዚሁ ለቃል ሲል በፈሪሳውያን አሳልፎ ሰጪነትና በጲላጦስ ፈራጅነት ተሰቅሏል። [3] እየሱስ ሲሰቀል እድሜው ሰላሳ አራት ነበር ይባላል። ቃሉ ግን ገና እስከ ዘላለም ይኖራል። ከክርስቶስ ልደት ከሁለት ሺህ

አንድ አመታት በኋላ የሰላሳ አራት አመቷ ብርቱካንም በአገር በቀል አረመኔዎች ትእዛዝ፣ በፈሪሳውያን አሳልፎ ሰጪነትና በእነጲላጦስ ፈራጅነት (እንሰሳ ሳይቀር ነጻ መውጣት በጀመረበት በሃያ አንደኛው ክፍለዘመን) ለቃል ስትል የአካላዊና የመንፈሳዊ ሰቆቃን መርዝ እንደ ሶቅራጥስ ሄምሎክ ጠጣች።

| | **ሶቅራጥስ** | **ክርስቶስ** | **ብርቱካን** |
|---|---|---|---|
| **የትውልድ ቦታ** | ግሪክ | ቤተልሔም | ጦቢያ |
| **በመጡበት ዘመን የኖሩበት አገር ሁኔታ** | ግፍ የበዛበት | ጭካኔና ክህደት የሰፈነበት | አረመኔነት፣ ስግብግብነት፣ ቅጥፈትና ክህደት ያገፈገፉበት |
| **ሙያ** | መምህር፣ ፈላስፋ | የምድሩም የሰማዩም ዳኛ | በምድር ዳኛ |
| **ስብከት** | ፍትህ | ፍትህ፣ፍቅር፣ ምህረት | ፍትህ፣ ፍቅር፣ አንድነት |
| **ለመከራ የዳረጋቸው** | ቃል | ቃል | ቃል |
| **የተቀበሉት መከራ** | በመርዝ መሞት | ስቅላት | የአካልና የመንፈስ ሰቆቃ |

እነዚህን ሶስቱን ከሚያለያዩአቸው በርካታ ጉዳዮች አንዱ ግፍ የፈጸሙባቸው ሰዎች ተፈጥሮ ነው። እኔ እስከማውቀው ድረስ የሶቅራጥስም ሆነ የክርስቶክ ገዳዮች ሴትን ልጅ ከጡት ወይም ከጡጦ ካልወጣች ልጇ ነጥለው አንዴም ሆነ ሁለቴ አላሰሩም። አምስት ወራት [4,5] ጨለማ ቤት በአካላዊና መንፈሳዊ ሰቆቃ ቶፋ ውስጥ አስገብተውም አልቀቀሉም። ፓትርያሪኩና ጳጳሱ ሳይቀር ክንዳቸውን አፈርጥመው፣ ትከሻቸውን አሳብጠው ቃልን እንኳን ከአካላቸው ከአገሪቱ በመጥረጊያ ጠርገው ሊያስወጧት በሚራራጡበት ወቅት ቃልን የምታከብር ባለማተብ ሴት ከቤተሰቧና በጠቅላላው ከአለም ገልለው ለአመታት በምድር የሲኦል ምጣድ ውስጥ አስገብተው አልጠበሱም። ታዲያ የሶቅራጥስ ሞት ለራሱ እንጅ ለገዳዮቹ እድሜ የቀጠለ አይመስለኝም። የክርስቶስ ሞት የራሱን እንጅ የፈሪሳውያንንና የጲላጦስን እድሜ አላረዘመም። የብርቱካን ሰቆቃም የእርሷን እድሜ እንጅ ያለ አንዳች ሰብአዊ ርህራሄ የጠበሷትን ከንቱዎች እድሜ አይቀጥልም። ዛሬም ቆመው እየሄዱ ሞተዋልና! ባጠቃላይ ሶቅራጥስ፣ ክርስቶስና ብርቱካን ሳልስት ፍትህ ሰባኪ! ቃል ጠባቂ! ዘላለማዊ!! አመሰግናለሁ።

ዋቢ


1. *The Republic; The story of philosophy, Will Durant 1926*
2. *Socrates: Stanford Encyclhopidia of Philosophy: http://plato.stanford.edu/entries/socrates/ (accessed on 9/28/2010)*
3. *የማትዮስ ወንጌል ምዕ ፳፯*
4. *Ethiopian Prisoner of Conscience Birtukan Mideksa Released/ Human Rights Watch http://blog.amnestyusa.org/iar/ethiopian-prisoner-of-conscience-birtukan-mideksa-released/ (accessed on 9/29/2010)*
5. *“መፈታቴን እንኳን ሰው ያውቃል ብዬ አልገመትኩም” አውራንባ ታይምስ 3ኛ አመት ቁጥር 136*


*ተመሳሳይ ጽሑፎች*

1. *ቃል የሚወጣውን ጭንቅላት አትንኩት* http://www.abbaymedia.com/Amharic/Chinkilat.pdf
2. *ሴቷን ማን እንበላት http://www.abbaymedia.com/Poems/Setuan.pdf*
3. *ሙያን እንደ ሹካ* http://www.quatero.net/pdf/Muyya.pdf

መስከረም ሁለት ሺህ ሶስት ዓ.ም.